ጥቂት ስለ ረመዷን እንተዋወስ

<u>በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው</u>

ክብርና ምስጋና አለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ውዳሴና ሰላም ለአለማት እዝነት በተላኩት በነብያችን ላይ፣ በባልደረቦቻቸው ላይና እነሱን በተከተሉት ላይ ይሁን።

የረመዷን ወር ሁሉም ሙስሊም በጉጉት የሚጠብቀው ወር ሲሆን ይህ ታላቅ ወር በውስጡ ብዙ መልካም ነገሮች ይዞ መቶልናል። የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ይሄ የተከበረ ወር ሲመጣ እንዲህ ይሉ ነበር "የረመዷን ወር መጣላችሁ። የተባረከው ወር። አላህ ወሩን መጾም ግዴታ አድርጎባችኃል። በእሱ ውስጥ የጀነት በሮች ይከፈታሉ የጀሀነም በሮች ይዘጋሉ። አመጸኛ ሽይጧኖች ይታሰራሉ። በእርሱ ውስጥ ከአንድ ሺህ ወር በላጭ የሆነችው ለይለቱል ቀድር ትገኛለች። የእሷን ትሩፋት ያላገኘ። ከመልካም ነገር እርም ሆኗል ።" (ኢማሙ አህመድ)

በሌላ ሐዲሳቸው " (በዚህ ወር) አላህ ከእሳት ነጻ የሚያደርጋቸው ሰዎቹ አሉ። ይሄም የሚሆነው በየለሊቱ ነው።" ብለዋል፡፡

በዚሁ በረመዷን ወር ለሰው ልጆች መመሪያ የሆነው ታላቁ ቁርአን ወረደ፣ል አላህ እንዲህ ይላል:-

شَهْرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِىٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلْقُرْءَانُ هُدًى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٍ مِّنَ ٱلْهُدَىٰ وَٱلْفُرْقَانِ

".. በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርአን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፡፡" (አል-በቀራ-185)

ከእስልምና አምስቱ ማዕዘናት አንዱ የረመዷንን ወር መጾም ነው። የአላህ መልዕክተኛ ﷺ "እስልምና በአምስት መሰረቶች ተገነባ። .."ብለው ከጠቀሷቸው አምስት መሰረቶች አንዱ የረመዷን ወርን መጾም ነው።

የረመዷንን ወር መጾም ሙስሊም በሆኑ፣ ለአካለ መጠን በደረሱ፣ የአዕምሮም ሆነ የአካል ጤነኛ በሆኑና መንገደኛ ባልሆኑ ላይ ባጠቃላይ ግዴታ ነው። ሴት ልጅ የወር አበባ ላይ ወይም የወሊድ ደም ካለባት መጾም የለባትም።

አላህ سبحانه وتعالى እንዲህ ብሏል

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ كُتِبَ عَلَيْكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡" (አልበቀራ-185)

<u>በረመዷን ልንሰራቸው የሚገቡ ተግባራት</u>

በረመዷን ወር ትልቁ ጭንቀታችን ወንጀላችን ተምሮ ከእሳት ነጻ መባል መሆን አለበት። በዚህ ወር አላህ በየለሊቱ ከእሳት ነጻ የሚላቸው ሰዎች አሉ። ከእነሱ ለመሆን መትጋት አለብን። ይሄን የተከበር ወር የሚገባውን ቦታ ሳይሰጡት ባልባሌ ነገር ልናሳልፈው አይገባም።

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ "ጅብሪል የረመዷን ወርን አግኝቶ ኃጢአቱ ሳይማርለት እሳት የገባ አላህ ከእዝነቱ ያርቀው አሚን በል አለኝ አሚን አልኩ። ብለዋል።" (ኢብኑ ሒባን)

በዚህ በተከበረ ወር ብዙ ልንተገብራቸው የሚችሉ ዒባዳዎች አሉ ከእነሱም ውስጥ

የለይል ሰላት (ተራዊህ) በረመዷን ልንተገብራቸው ከሚገቡ ዒባዳዎች ነው። የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል:- "የረመዷንን ወር አምኖና (ምንዳውንም) ለማግኘት ነይቶ (በዒባዳ) የቆመ ሰው ከዚህ በፊት የፈጸማቸው ወንጀሎች ይማራሉታል።" (ቡኻሪና ሙስሊም)

የተራዊህን ሰላት ኢማሙ እስኪቸርስ አብሮ የሰገደ ሰው ለሊቱን ሙሉ እንደሰገደ ይቆጠርለታል የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል:- "ኢማሙ እስኪያጠናቅቅ ከኢማሙ ጋር የቆመ (የሰገድ) ለሊቱን ሙሉ እንደሰገደ ይጻፍለታል።" (ነሳኢና ኢብን ማጃህ ዘግበውታል)

ቸር መሆን:- ከሌላ ጊዜ በተለየ መልኩ የተቸገረን መርዳት፣ ጾመኛን ማስፈጠር፣ እዳ ያለበትን ከቻልን እዳውን መክፈል… ሌሎችንም መልካም ስራዎች ለሌሎች ማድረግ በረመዳን በይበልጥ ከሚሰሩ መልካም ስራዎች ውስጥ ነው። ዐብደላህ ኢብኑ-ዐባስ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) እንዲህ ይላል:- "የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ከሰዎች ሁሉ በላይ ቸር ነበሩ፡፡ ይበልጥ እጅግ ቸር ይሆኑ የነበረው በረመዷን ጅብሪል በሚገናኛቸው ወቅት ነበር፡፡.." (ቡኻሪና ሙስሊም)

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ በሌላ ሐዲስ "ጾመኛን ያስፈጠረ ካስፈጠረው ሰው አጅር ሳይቀነስ ያስፈጠረውን ሰው ተመሳሳይ አጅር (ምንዳን) ያገኛል።" ብለዋል። (ቲርሚዚ)

ቁርአን መቅራት በረመዳን ይበልጥ ከሚወደዱ ተግባራት ነው። ነብያችን ﷺ በረመዳን በእያንዳንዱ ለሊት ከጅብሪል ዐለይሂ ሰላም ጋር ቁርአንን ይማማሩ ነበር። ዐብደሏህ ኢብን ዐባስ ረዲየሏሁ

ዐንሁማ "ጅብሪል በየለሊቱ (በረመዷን ወር) የአላህ መልዕክተኛን ይገናኛቸውና ቁርአን ይማማሩ ነበር።" **ብላል** (ቡኻሪና ሙስሊም) ከሰለፎች ረመዷንና ቁርአንን በተመለከተ ብዙ ዘገባዎች መተዋል፡፡ ከእነሱ ውስጥ በረመዷን ቁርአንን ስልሳ ጊዜ የሚጨርስ ነበር፣ ከእነርሱ ውስጥ ቁርአንን በየቀኑ፣ በየሁለት ቀኑ፣ በየሶስት ቀኑ፣ በየሰባት ቀን.. ያኽትሙ እንደነበር ተዘግቧል። እኛም በዚህ በተከበረ ወር የቻልነውን ያህል መቅራት አለብን። ቁርአንን መቅራት ብቻ ሳይሆን በቻልነው አቅም ትርጉሙንና መልዕክቱን ለማወቅ መጣር አለብን።

ሱሁርን አዘግይቶ መመገብ ሌላው ተወዳጅ ተግባር ነው። የአላህ መልዕክተኛ ﷺ "ኡመቶቼ ሱሁርን እስካዘገዩ ድረስ ከመልካም ነገር አይወገዱም።" ብለዋል። (አሕመድ) ሱሁርን መመገብ በራሱ በረካ ያለው ተወዳጅ ተግባር ነው። የአላህ መልዕክተኛ ﷺ "ሱሁርን ተመገቡ በሱሁር ውስጥ በረካ አለ። ብለዋል።" (ቡኻሪና ሙስሊም) በተቃራኒ ኢፍጣርን ማቻኮል ደግሞ ሌላው ተወዳጅ ተግባር ነው የአላህ መልዕክተኛ ﷺ "ሰዎች ፍጡርን እስካቻኮሉ ድረስ ከመልካም ነገር አይወገዱም።" ብለዋል። (አሕመድ) ፍጡርን ከተገኘ በቴምር መጀመር ከሌለ ደግሞ በውሃ መጀመር ሱና ነው።

የመጨረሻዎቹ አስር ቀናቶች ላይ ይበልጥ በዒባዳ መጠንከርና ለይለቱል ቀድርን መጠባበቅ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እና የሰለፎች ተግባር ነው። ረመዳን ሊያልቅ አስር ቀናቶች ሲቀሩ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ አስሩንም ቀን በኢዕቲካፍ (መስጂድ ውስጥ ለዒባዳ ጠቅለል ብሎ በመግባት) ያሳልፉ ነበር።

ለይለተል ቀድር ከአንድ ሺህ ወር በላጭ የሆነች ቀን ናት። ይሄንንም አላህ በቁርአኑ እንዲህ ሲል ነግሮናል

لَيْلَةُ ٱلْقَدْرِ خَيْرٌ مِّنْ أَلْفِ شَهْرٍ

መወሰኛይቱ (ለይለቱል ቀድር) ሌሊት ከሺሕ ወር በላጭ ናት፡፡

ነብያችን ﷺ "ለየለቱል ቀድርን አምኖበትና ምንዳን ፈልጎ የቆመ (የሰገደ) ከዛ በፊት የሰራው ኃጢአት ይማርለታል።" ብለዋል (ቡኻሪ)

<u>ረመዷን የተውበት ወር</u>

የረመዷን ወር የአላህን ባርነት ዘንግቶ ለስሜቱ ባሪያ ለሆነ፥ በዱንያ ጭንቀት አኼራን ለረሳ፥ ሞትን ረስቶ በወንጀል ባህር ለሰመጠ፣ ከአላህ ፍላጎት ይልቅ የነፍሱን ፍላጎት ላስቀደመ፣ ከቁርአን ይልቅ ዘፈንን ለመረጠ፣ ከዚክር ይልክ በሐሜት ለተዘፈቀ፣ ከሐላል ይልቅ ሐራምን ለመረጠ፣ በሐራም የፍቅር ጓደኝነት ለተፈተነ፣ በተለያዩ ሱሶች ጌታውን ላመጸ በቃኝ ብሎ ወደ አላህ ለመመለስ ጥሩ አጋጣሚ ነው። የአላህ ምርጥ ባሮች በዚህ ወር በዒባዳ ይበልጥ የሚጠነክሩበት ጊዜ ነው። ኃጢአተኞችም በዚህ ወር ወደ ነበርንበት የወንጀል ባህር ላለመመለስ ቆርጠን በኑህ የመዳን መርከብ

እስከመጨረሻው ልንሳፈር ይገባል። ታዲያ ተውበት ስናደርግ ልናሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶች አሉ። እነዚህ መስፈርቶች ካልተሟሉ ተውበታች ተቀባይነት አይኖረውም።

1ኛ ተውብቱ ለአላህ ብቻ ታስቦበት ሊሆን ይገባል። ሌሎች ዱንያዊ ነገሮች የታሰቡበት መሆን የለበትም

2ኛ ወንጀሉን ማቆም አለብን

3ኛ ወንጀሉን ከዚህ በፊት በመስራታችን መጸጸት አለብን

4ኛ ወንጀሉን ዳግም ላለመስራት ቆራጥ መሆን አለብን።

5ኛ ተውብቱ ሞት ጫፍ ላይ ከደረስን በኃላና ጸሀይ በመግቢያው ከመውጣቷ በፊት መሆን አለበት

6ኛ የሰራነው ወንጀል የሌሎችን ሐቅ በመንካት ከሆነ ሐቃቸውን መመለስ ወይም ይቅርታ ማስደረግ ናቸው። እነዚህ መስፈርቶች ካልተሟሉ ተውበት ተቀባይነት አይኖረውም።

<u>ከረመዳን ጋር የተያያዙ አንዳንድ አሕካሞች</u>

የረመዷን ጾም ገዴታ የሚሆነው ሙስሊም በሆነ ለአካለ መጠን በደረሰና የአካልም ሆነ የአዕምሮ ጤነኛ በሆነና መንገደኛ ባልሆነ ሰው ሁሉ ላይ ነው። ሴት ልጅ ለመጾም ከወር አበባና ከወሊድ ደም የነጻች መሆን አለባት። የወር አበባ ላይ ወይም የወሊድ ደም እያለባት ብትጾም ጾሟ ተቀባይነት የለውም። በዚህ ምክንያት ያልጾመቻቸውን ቀናቶች በኃላ ላይ ቀዳ ታወጣለች።

<u>ጾምን የሚያፈርሱ ነገራቶች</u>

1/ መብላትና መጠጣት እንዲሁም ምግብን የሚተካ መርፌና ጉልኮስ መውሰድ። ሌላ የመድሃኒት መርፌና የስኳር ኢንሱሊን መውሰድ ግን አያፈርስም ከተቻለ እነዚህን ማታ ላይ ማድረጉ ይመረጣል'

2/ መጨረሻ ላይ ባያደርጉት እንኳ ጾምን ለማፍረስና ለመብላት ወይም ለመጠጣት እንዲሁም ሌሎችን ጾም የሚያፈርሱ ነገሮችን ለማድረግ መወሰን

3/ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም (የወንድ ሀፍረተ-ገላ ከሴት ልጅ ሀፍረተ-ገላ የውስጠኛው አካል ጋር ከተነካካ:-የዘር-ፈሳሽ ባይወጣ እንኳ የሁለቱም ጾማቸው ይፈርሳል)

4/ ያለ ግብረስጋ-ግንኙነት እንኳ ቢሆን በራስ ፍላጎት (ስሜትን የሚቀሰቅስ ነገር ደጋግሞ በማየት፣ ከተቃራኒ ጾታ ጋር በስሜት በማውራት፣ ብልትን በመነካካት ወዘተ) የዘር-ፈሳሽ ማስወጣት' በተኛበትና ያለፍላጎቱ የዘር-ፈሳሽ የወጣው ሰው ግን ጾሙ አይፈርስም

ልብ ይበሉ! ከዘር ፈሳሽ ውጪም ያሉ በስሜት መቀስቀስ ምክንያት የሚወጡ ፈሳሾች ጭምር ጾምን እንደሚያፈርሱ ኢማም አሕመድን ጨምሮ የተወሰኑ የዲን ሊቃውንት ገልጸዋልና ይጠንቀቁ!

5/ የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም መፍሰስ።

6/ በዋግምት፣ ደም በመለገስና በመሰል መንገዶች ብዛት ያለውን ደም ከሰውነት ማስወጣት'

ይህ በዲን ሊቃውንት መሀል ኺላፍ ቢኖርበትም ጾም ያፈርሳል በሚለው መሄድና መጠንቀቁ የተሻለ ነው።

❖ለምርመራ ደም መስጠት ግን ችግር የለውም

7/ ፈልጎና ሆን ብሎ ማስመለስ' ይህ የ4ቱም የዲን መሪዎች ምርጫ ሲሆን ማስረጃቸው "ሆን ብሎ ያስመለሰ ቀዳ ያውጣ፣ ሳይፈልግ ያስመለሰ ምንም "ቀዳ"የለበትም የሚለው የሰሓቢዩ ኢብኑ ዑመር ንግግር ነው' በዚህ ላይ ምንም እንኳ ከነቢያችን صبى الله عليه وسلم የተነገረ ሰሒሕ ሐዲስ ባይኖርም ቢያንስ ከኺላፍ ለመራቅ ብለን ልንጠነቀቀው ይገባናል።

ከሰበቡ አንዱ ምግብ ማብዛት ነውና ምግብና መጠጥ አያብዙ!

በመጨረሻም፦ ምራቅን መዋጥ ጾም አያፈርስም

አኽታ ምራቅ ቆሻሻና ጎጂ ከመሆኑ አንጻር እሱን መዋጥ የተከለከለ ነው።

- ከላይ የተጠቀሱ ነገሮች በሙሉ ጾም የሚያፈርሱት:-

1/ ጾምን እንደሚያፈርሱ እያወቁ

2/ ረስተው ሳይሆን እያስታወሱና እያወቁ

3/ ተገደው ሳይሆን በሙሉ ፍላጎት ካደረጓቸው ብቻ ነው ጾም የሚፈርሰው። ረስቶ ወይም ባለማወቅ ወይም ተገዶ ከነዚህ አንዱን ያደረገ ሰው ጾሙ አይፈርስም እንዳወቀ መታቀብና ጾሙን መቀጠል ብቻ ነው የሚጠበቅበት። ወላሁ አዕለም (ከኡስታዝ አሕመድ ኣደም ጽሁፍ የተወሰደ)

አንድ ሰው በረመዷን በቀኑ ክፍል ጊዜ ከባለቤቱ ጋር ጾታዊ ግንኙነት ማድረግ ወንጀል ሲሆን። በዚህ ምክንያት ጾሙን ያፈረሰ ሰው ባሪያን ነጻ ማወጣት ካልቻለ ሁለት ወር በተከታታይ መጾም ካልቻለ ደግሞ ስልሳ ሚስኪኖችን ማብላት እንዲሁም ተውበት ማድረግ አለበት። የዛን ቀንም ጾሙን ይሞላል በኃላ ላይም ቀዳ ማውጣት አለበት።

<u>በረመዷን መብላት የሚፈቀድላቸው ሰዎች</u>

1ኛ በእርጅና ምክንያት መጾም የማይችሉ ሽማግሌዎች ወይም ይድናሉ ተብሎ ተስፋ የማይጣልባቸው ህመምተኞች በረመዳን ማፍጠር (አለመጾም) ይፈቀድላቸዋል ለእያንዳንዱ ቀንም ሚስኪን ያበላሉ።

2ኛ ረዥም ርቀት የሚጓዝ መንገደኛ ከፈለገ መጾም ካልፈለገ ማፍጠር (አለመጾም) ይችላል። መንገደኛ በመሆኑ ምክንያት ያልጾማቸውን ቀናቶች በኃላ ላይ ቀዳ ያወጣል።

3ኛ ይድናል ተብሉ ተስፋ የሚደረግበት ህምምተኛ ሰው መጾሙ የሚከብደው ከሆነ ማፍጠር (አለመጾም) ይችላል። ህመሙ በመጾሙ ምክንያት ይብልጥ የሚጎዳው ከሆነ መጾም ይከለከላል። ያፈጠረባቸውን ቀናቶች በኃላ ላይ ቀዳ ያወጣል።

4ኛ እርጉዝ ወይም የምታጠባ ሴት መጾሟ እሷ ላይ ወይም ልጇ ላይ ጉዳት ይደርሳል ብላ ከፈራች ማፍጠር (አለመጾም) ትችላለች። በኃላ ላይ ያልጾመቻቸውን ቀናቶች ቀዳ ታወጣለች።

5ኛ የወር አበባ ላይ ወይም የወሊድ ደም ላይ ያለች ሴት ጾም ትከለከላለች። ያልጾመችባቸው ቀናት በኃላ ላይ ቀዳ ታወጣለች።

6ኛ ለአካል መጠን ያልደረሱ ልጆች ጾም ግዴታ አይሆንባቸውም። ልጆች ለአካለ መጠን እስኪደርሱ ወላጆች ማለማመድ አለባቸው።

7ኛ የአዕምሮ ህምምተኛ ጾም የለበትም።

ወሏሁ አዕለም

<u>ረመዷን ላይ የሚስተዋሉ ስህተቶች</u>

- ከሚፈለገው በላይ ምግብ በመስራት ምግብን ማባከን
- አብዛኛውን ጊዜ ምግብ በመስራት ማሳለፍና ለዒባዳ ጊዜ ማጣት በተለይ እህቶች
- ቀኑን ሙሉ ተኝቶ የዙሁርና የዐስር ሰላት ወቅትን ማሳለፍ። የግዴታ ሰላቶችን ወቅታቸው እስኪወጣ ማዘግየት ከትላላቅ ወንጀሎች ውስጥ ነውና አላህን ፈርተን በወቅቱ መስገድ አለብን።
- ሱሁርን እኩለ ለሊት ላይ በልቶ በዛው በመተኛት የፈጅር ሰላትን ጸሀይ እስከምትወጣ ድረስ ማዘግየት ከትላልቅ ወንጀል ሲሆን በረመዷን ከሚታዩ ጥፋቶች ነው
- ከተራዊህ መልስ ዒባዳ የሌለ በሚመስል መልኩ በፊልም፣ ተሰባስቦ ሰዎችን በማማት፣ ሐራም ነገሮችን በመመልከት የለሊቱን ወርቃማ ጊዜ ባልተፈቀዱ ነገሮች ማሳለፍና ሌሎች በረመዳን የሚታዩ ስህተቶች አሉ። ሁላችንም ራሳችንን ከእነዚህ ተግባሮች ቆጥበን ለዚህ ታላቅ ወር ተገቢውን ቦታ በመስጠት በዒባዳ ላይ ልናሳልፈው ይገባል በማለት ራሴንና እናንተን እመክራለሁ።

አላህ የረመዷንን ወር በአግባቡ ተጠቅመውበት ከሚያልፉ ያድርገን አሚን